# እኛ እንተባበር-
# ይህን ሕግን የሚንቅ ሥርዓት ማስወገድ እንችላለን !

ግርም ካሳ (ቺካጎ)
muziky68@yahoo.com

ታህሳስ 24 ቀን 2001

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ዋሽንግተን ዲሲ የአንድነት ፓርቲ ልኡካን ቡድን አባል ሆነዉ ለኢትዮጵያዉያን ንግግራቸዉን ሲጀምሩ በጸሎት ነበር የጀመሩት። «አምላክችን ሆይ ኢትዮጵያ ተችግራለች። እኛም ተችግረናል። እባክህ ፍቅርን ስጠን» ብለዉ እግዚአብሄርን ሲማጸኑ ከአይኖቼ እንባ ፈሶ ነበር። በኢንተርኔት ብቻዬን እከታተል ስለነበረም ድምጼን ከፍ አድርጌ «አሜን !» ብዬ ጮህኩኝ።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ከቃሊቲ እሥር ቤት በተፈቱ ጊዜ በጀርመን ድምጽ ሬዲዮ ጋር ያደረጉት አንድ የማልረሳዉ ቃለ መጠይቅ ነበር። «ስላሰሯቹህ ስዎች ምን ትላላቹህ። እንደጠላት ነዉ ወይ የምታይዋቸዉ ?» ተብለዉ ሲጠየቁ «ቅንጅት የሰዉ ጠላት የለዉም» በማለት ነበር እርሳቸዉና አብረዋቸዉ የታሰሩ ጓደኞቻቸው በጥላቻና በቂም በቀል ያልተሞሉ ከራሳቸዉ ጥቅም ይልቅ በኢትዮጵያ መረጋጋት ሰላምና እርቅ እንዲመጣ የሚፈልጉ መሆናቸዉን ያሳዩን።

የቀድሞ ቅንጅት አሁን አንድነት አመራር አባላት በዳያስፖራ ካሉ አንዳንድ አካላት ከፍተኛ ተቃዉሞ እየደረሰባቸዉም ቢሆን «ወያኔ ጠላት አይደለም። የምናደርገዉ ትግል ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያን ለመጥቀም አላማዉ ያደርገ ትግል እንጂ ጸረ ወያኔም ሆነ ጸረ ማንም ትግል አናደግርም።» እያሉ በድፍረት ሕዝቡን አስተምረዋል።

እኛም የነዚህን ሰላማዊ የዲሞክራሲ ጀግኖች ጥሪ ተከትለን አብረናቸዉ የሰላም የእርቅ የወንድማማችነትና የፍቅር መልዕክት ስናስተጋባ ቆይተናል። «አሁን በስልጣን ላይ ካሉት ጋር መነጋገርና መወያየት ያስፈልጋል። እነርሱን መለወጥ እንችላለን» በሚል ነጩን የሰለም ባንዲራ አዉለብልበናል። ምላሹ ግን መሪዎቻችንን በሰደፍ መደብደብና በግፍ ቃሊቲ ማወረድ ሆነ።

አዎ መስሎን ነበር በአራት ኪሎ ያሉ ባለስልጣናት የሚሰሙን። መስሎን ነበር አይሞሮና ልብ ያላቸዉ። መስሎን ነበር ከዚህ በፊት ከሚሄዱበት መንገድ ሊመለሱ የሚችሉ።

ከጊዜ ወደ ጊዜ የምናየዉ ግን ተስፋ የምናደርገዉን ሳይሆን አንገታችን የሚያስደፋዉን ነዉ። ልባችንን በደስታ የሚሞላ ሳይሆን ዉስጣችንን የሚያቆስል ነዉ። ፍቅርና ይቅርታን የሚያወሩ እነ ቴዲ አፍሮ በግፍ ሲታሰሩ፣ የሰላምና የስብዓዊ መብት መከበር ሐዋርያ የሆኑት እነ ፕሮፌሰርን መስፍንን ወልደማሪያም ሲደበደቡ፣ ለፍትህና ለኢትዮጵያ አንድነት የቆሙ እነ በርቱካን ሚደቅሳ ወህኒ ሲጣሉና የጭካኔ የዛቻ የትዕቢት የዉሸትና የሸፍጥ ፖለቲካ እየበዛ ሲሄድ ነዉ የምናየዉ።

የአሜሪካን ድምጽ ሬዲዮ ባልደረባ አቶ ሰለሞን ክፍሌ ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ጋር ያደረጉትን ቃለ መጠይቅ ሳዳምጥ ሐዘን ብቻ አልነበረም የተሰማኝ ሐፍረትም እንጂ።

ተሸማቀኩኝ። «ኢትዮጵያዊ ናቸዉ። የኔ ወንድሞች ናቸዉ» የምላቸዉ ወገኖች እንዲህ አይነት ሥራ ሲሰሩ ሳይ «ምን አይነት ትዉልድ ሆነናል!» ብዬ አዘንኩኝ።

እስቲ አስቡት ! የሰባ ስምንት አመት አዛዉንትን በሰደፍ መደብደብ ስብዕና ይባላል ? አዉሬነት እንጂ። እስቲ አስቡት ! አንዲትን ሴት በአራት መኪናና በአሥር ደህንነቶች እያዋከቡ እያንገላቱና እየገፉ መንዳት ሕግን ማክበር ይባላል ? ውንብድና እንጂ።

ኢሕአዴግ ዉስጥ ጥሩ ልብ ያላቸዉ ፓርቲዉን ወደ ቀናዉ መንገድ ሊመሩት የሚችሉ ሊኖሩ ይችላሉ የሚል ተስፋ ነበረኝ። አሁንም እነዚህ ሰዎች አሉ ብዬ አስባለሁ። ነገር ግን በዚህ ሳምንት ከታየዉ አሳዛኝ ሁኔታ አንድ በግልጽ የደረስኩበት ድምዳሜ አለ። **እርሱም ኢሕአዴግን ወደ ጥሩ አቅጣጫ ሊወስዱ የሚችሉ ኃይላት በፓርቲዉ ዉስጥ ምንም ለዉጥ ሊያመጡ እንዳልቻሉና በነርሱ ተስፋ ማድረግ ከአሁን በኋላ የሚያዋጣ እንዳልሆነ እየታየኝ ነዉ።**

«ታዲያ ምንድን ነዉ የሚያዋጣዉ? » ብላቹህ ብትጠይቁኝ በቀዳሚነት አንድ ነገርን አጉልቼ እናገራለሁ። **መፍትሄዉ የሚያዋጣዉ በአንዲት ኢትዮጵያ የምናምን በአገራችን ዲሞክራሲ እንዲሰፍን የምንሻ ሁሉ በቅንነት እርስ በርስ ከመጠቃቃት ተቆጥበን በሚያስማሙን ነገሮች ላይ መተባበሩ ብቻ ነዉ።**

ለዚህም እንዲረዳ የሚከተሉትን ነጥቦች ለፖለቲካ ሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶችና ለሚዲያ ግሩፖች በአክብሮት አቀርባለሁ፡

1. እያንዳንዱ ድርጅት ሌላዉን ከመንቀፍ ተቆጥቦ በሚሰራዉ ሥራ ላይ ያተኩር። በሥራዉ ዉጤት የሚያመጣ ድርጅት ምንም በሌሎች ቢተችም በሕዝብ መደገፉ አይቀሬ ነዉ። **ኢትዮጵያዉያን ወሬ ሳይሆን ወጤት ነዉ የሚፈልጉት።**

2. በሌሎች ድርጅቶች የድጋፍ ካልሆነ የጥቃት መግለጫ ማዉጣት፣ የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎችን መሳደብ ይብቃ።

3. በመግለጫዎቻችን በሚዲያዎቻችን የምናወጣቸዉ በእዉነት ላይ የተመሰረቱ ያልተለጠጡና ያልተጋነኑ ይሁኑ ! የሰለጠን ስብእና ያለን ጨዋ ኢትዮጵያዋያን መሆናችንን በዚህ እናሳያለን።

4. «የሰላማዊ ትግል አይሰራም፤ የትጥቅ ትግል አይሰራም» እያልን መከራከራችንን እናቁም። እኔ ሰላምዊዉ ትግል የሚበጅ አማራጭ ነዉ እላለሁ። ይህ አቋሜ ይከበርልኝ። «አይ ወያኔ በጠመንጃ ካልሆነ አይቻለም» የሚሉ ደግሞ እነርሱ ይዘናል ባሉት መንገድ ይቀጥሉበት። አቋማቸዉ ይከበርላቸዉ። «ይሄ ይበጃል ያ ይበጃል» የሚለዉን ክርክር ሂደት የሚወስነዉ ይሆናል።

5. ሕብረት መፍጠሩ ጠቃሚ ቢሆንም በችኮላ ሕብረት መፍጠሩ ጉዳት ሊያመጣ ይችላል። ሕብረት መፍጠሩ ላይ አሁን ከማተኮር ቢያንስ ቢያንስ በጋራ የሚሰሩ ሥራዎች ላይ አብሮ የመስራትን ባህል ማዳበር ይጠቅማል። የጋራ ሕዝባዊ ሰላማዊ ሰልፎችን ለማድረግ፣ የጋራ መግለጫዎችን ለማዉጣት ያስችል ዘንድ ከሁሉም ወገን የተወጣጣ አንድ ግብረ ኃይል፣ የዲፖሎማሲዉን ሥራ በቅንጅት የሚሰራ ሌላ ግብረ ኃይል በአስቸኳይ እንዲቋቋም ያስፈልግሃል። ሥራዉ አንድ አይነት ሆኖ በአሥር ገመድ በተለያዩ

ድርጅቶች መነተት የለብንም። አሜሪካኖች አዉሮፓዊያኖችም ቢሆኑ ከሃያ ድርጅቶች መስማት አይፈልጉም። በአንድ ድምጽ ካልተናገርን ይንቁናል።

ዉድ ኢትዮጵያዉያን እነብርቱካን ሚደቅሳ በቃሊቲ እየተሰቃዩ ነዉ። እነ ፕሮፌሰር መስፍን ሰደፍ አርፎባቸዋል። ያለፉትን ልዩነቶቻችን አቻችለን ከዚህ በፊት ለተነጋገርነዉና ለተቀያየምነዉ ይቀር ተባብለን ለአንዲት ኢትዮጵያ በጋራ ለመስራት ክብራችን መዋጥ ያቅተናልን ? አያቅተንም። እንችላለን።

ትንሹ ዳዊት ግዙፉን ጎሊያድ ጥሏል። እኛ ከተባበርን እኛ ከተደጋገፍን የማንወጣዉ ተራራ የለም። እኛ እንተባበር ፤ በርግጥ ይህ ሕግን የሚረግጥ ሥርዓት ሲወገድ እናያለን። ጥያቄው «እንችላለን ወይ? » አይደለም ? ጥያቄዉ «ፍላጎቱ አለን ወይ? » የሚል ነዉ።